ፓኖራማ ቁጥር 72

የትዝብት አድማስ

ሰኔ 14 ቀን 2001 ዓም

## ታሪክ ሆደ ባሻ አይደለም

ታሪክ እስከቆየ ፥ እስከ ተጠበቀና እስከ ተከበረ ድርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፉ የማይቀር ነው ። ተረካቢው ትውልድ በበኩሉ የተረከበውን ታሪክ ጠብቆና አክብሮ ለሚቀጥለው ትውልድ እስካላስረከበ ድርስ ግን ታሪክ በሂደት ይጠፋል። ታሪክ እስከ ጠፋ ድረስ ደግሞ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ሀገርም እንደ ሀገር ቀስ በቀስ የማይጠፋበት ምክንያት አይኖርም። ይህ ክስተት በዛሪይቱ ኢትዮጵያ በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየተከናወነ ለመሆኑ ማስረጃ አምጡ የሚባልለት አይደለም። ማነኛውንም ውጣ ውረድ ተቋቁሞ፥ ታሪክ ህያው እስከሆነ ድርስ ግን ፥ ከፋኝ ተበደልኩ በሚል ብቻ ምስክርነቱን ከማስረዳት ወደኋላ አይልም ። በሆደ ባሻነት ተሸብቦ የነበረውንና ያለውን ከመመስከር አይታብይም ። ሀገርና ሕዝብ ከጠፉ፥ የታሪክም ልሳን አብሮ መዘጋቱ አይቀርም ። ያ ከሆነ ደግሞ ፥ የሀገርን ብሥራት ቀርቶ መርዶውን እንኳን የሚናገር አይኖርም ። የዓለም ታሪክ መመዝግብ ከጀመረበት አንስቶ ያለውን ሂደት ለአስተዋለ ሰው በርካታ ሀገሮች ከነሕዝባቸውና ታሪካቸው ደብዛቸው ጠፍቶ መቅረቱን ይገነዘባል ። የዚህ ሰለባ የሆኑ ሕዝቦችና ሀገሮች ቋንቋቸው ፤ ባህላቸውና ዕምነታቸው ወድሟል ። ኃይለኛው ደካማውን በጦር ኃይል እየደመሰሰ የራሱን ባህልና ቋንቋ ፥ ታሪክና ዕምነት እየተካ በኃይል የያዘውን ሀገርና ሕዝብ ማንነት ያወድማል።

" ኃይለኛ እየሄደ ያስገብራል የትም ፥ መሬት የጀግና እንጅ ባለቤት የላትም ። " የሚለው የቅኝ ገዥዎችና ሀገር ወራሪዎች የዘመቻ መዝሙር የጦር ሠራዊታቸው የክተት አዋጅና የሰልፍ እርምጃ ሙዚቃ እየሆነ ቆይቷል ። ዛሬም ይህ የዘመቻ መዝሙር የባለ ጊዜዎችና የወራሪዎች የጦርነት ሰልፍና ጉዞ ቃና ሆኗል ። እነዚህ ባላጊዜዎች የነዋሪዎችን የቆየ ታሪክና ባህል ፥ ማንነትና ሰብዓዊ ተፈጥሯቸውን ለማጥፋት ከሚጠቀሙባት የመጀመሪያ ርምጃቸው ፥ ታሪክ አዋቂዎች ናቸው ብለው የሚጠረጥሯቸውን አዛውንትና ምሁራን ደብዛቸውን ማጥፋት ይሆናል ። ታሪክና ሀቅ የሚያውቁትንም ዘልፎና ወንጅሎ አብጠልጥሎና አስጠልቶም ሰሚ ማሳጣት ሌላው ዘዴያቸው ነው ። የማነኛው ሀገር መሠረቱ የዚያው ሀገር ዜጋ እንደመሆኑ ፥ ዜጋውን ፥ የሀገሪቱን ነዋሪ አጥፍቶ መሬቷን ባዶ ማድረግ


Ethiopia will prevail !

ለቅኝ ግዛት ዋስትና ይሰጠናል ብለው ያምናሉ ። የአንድን ሀገር ነዋሪ በዘርና በክልል መከፋፈልም ከዚህ የተለይ ሁኖ ሊታይ የሚገባው አይሆንም ። ከፋፍለህ ገዛው የሚለው የቀድሞው የቅኝ ግዛት ፖሊሲ ፥ በዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ገዥ ነን ባዮች ፥ ከፋፍለህ ግዛ ብቻ ሳይሆን ፥ አዳክመህ አጥፋ የሚል ፖሊሲ ታክሎበታል። የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያካሂዱት የታሪክ፥ የባኅል፥ የዕምነትና የሕዝብ ውድመት ሂደቱ ሀገሪቱን ጨርሶ ለማውደም ከሚደረገው ዓላማ ጨርሶ በተለይ መልኩ ሊገመገም አይችልም ። የሀገርን መጥፋት አደጋ አስቀድመው በማወቅ ስጋታቸውን የገለፁ አዛውንትና ታጋዮች ዛሬ ደብዛቸው እንደጠፋ ምን ያህሉ ዜጋ እንደተረዳውም ማወቅ ቀላል አይደለም።

በሀገራቸው በኢትዮጵያ ላይ የሚያንዣብበውን የጥፋት አደጋ አስቀድመው ከተናገሩት ምሁራን መካከል አንዱ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ፥ ከጥቂት አሥርተ ዓመታት በፊት በሚከተሉት ቃላት ስጋታቸውን በጽሁፍ አስፍረው እንደነበር መጽሃፋቸውን ያነበበ ሁሉ ያስታውሰዋል። ደራሲ ብርሃኑ ድንቄ እንዲህ ብለው ነበር። እንጠቅሳለን ፦

" አገራችን ኢትዮጵያ፥ምንም እንኳ ዛሬ አርጅታ፥ደህይታ፥ያለልክ ተዳክማና የውርጋጦች መሳገጫ ሆና ብትታይ ፥ በረዢም ዘመናት ውስጥ የታሪካችን አበባ ለማኅበራዊ ሕይወታችን ልዩ ጌጥና ድምቀት በመስጠት የሚያኮሩ የታላላቅ ጀግኖች እናት አገር እንደነበረች አይካድም። "

ይህ ጥቅስ የተወሰደው፥አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የአፄውን ሥርዓት በመቃወም በፈቃዳቸው ሹመታቸውን ከለቀቁ በኋላ ከደረሷቸው አያሌ መጸሀፍት መካከል <u>ኤርትራዊ አስገዶም</u> ለተሰኘው መጽሀፋቸው መግቢያ እንዲሆናቸው፥

"ምንም ብታረጅ ያች እናት
የጎበዞች ወላጅ እኮ ናት። "

ከሚለው ጽሁፍ ስር ነው።የሀገራቸውን የወደፊት መልካም ራዕይና ተስፋ የሚመኙ ታላላቅ ዜጎች፥ደራሲያን፥የታሪክ ሊቃውንት፥ ሀገር-ወዳድ ምሁራን፥አርበኞች፥ ተራማጅ ትውልድ የሃይማኖትና የባኅል ተቋማት ፥ የሥነ ጥበብና የሥነ ጽሁፍ ሰዎች ወዘተ... በየታሪክ አጋጣሚዎች ሁሉ አስመዝግበው ያለፏቸው በርካታ የታሪክ ማስታወሻዎችና የሀገር ቅርሶች ሞለተዋል ። በአሁኑ ወቅት ይጥፉ ይዳኑ ግን በትክክል መናገር የሚቻል አይሆንም ። ሀገራችን አሁን ያጋጠማትን ችግርና የኅልውና አደጋ አስቀድመው በመረዳት ስጋታቸውን የገለጹትን ሁሉ መመዝገብ ባይቻልም ፥ ለአብነት ያህል ጥቂቶችን መጥቀስ አግባብነት ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፥ ይህ የዛሬው ትውልድ ውለታ ቢስ አለመሆኑንም ያስረዳል እንላለን ። ግርማቸው ተክለ ኃዋርያት፤ ከበደ ሚካኤል፥ ሀዲስ ዓለማየሁ፥ ሎሬት ፀጋየ ገ / መድኅን ፥ገሪማ ታፈረ፥ አቤ ጉበኛ ፥ከደራስያን መካከል በፋና ወጊነት የሚጠቀሱ ናቸው ።

ሌሎቹን ሁሉ ለመጥቀስ የዚህ ሐተታ አምድ ስለሚጠብ ለጊዜው ብንታቀብም፥ ወደፊት እንደ አስፈላጊነቱ በታሪክና በትግል ሂደት መጥቀሳችን አይቀርም ። ምክንያቱም ትግላችን የሀገራችንና የሕዝባችንን ዘላቂ ራዕይና ፥ ሁለንተናዊ የሆነውን ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ዓላማ ያደረገ በመሆኑ ነው ። በድርጅት ደረጃ ደግሞ ኢሕአፓ ኢትዮጵያን ለማስከበር የተጋለውና የከፈለው መስዋዕትነት የሚጠቀስ ነው።

የማነኛውም ሀገር ሕዝብ ታሪክ አውነታዊና አሉታዊ ገጽታዎች እንዳሉት የታወቀ ሆኖ እያለ፥ እናም ደግሞ ታሪክን በታሪክነቱና በሁለንተናዊው መልኩ መገምገምና መተንተን ሲገባ፥ የሀገራችን የወቅቱ ገዥዎች ግን የኢትዮጵያን አሉታዊ ገጽታ ብቻ ነጥሎ በማውጣት ለጥላቻቸው ማጠየቂያና ለጥፋታቸው ማካሄጃ ይጠቀሙበታል። ለዚህ እኩይ ተግባራቸው መሠረት ይሆነናል ብለው የሚያተኩርበት፥ የኢትዮጵያን የብዙ ብሄር-ብሄረስብ ገጽታና የሃይማኖቶችን ልዩነት ነው።የወያኔ መሪዎችያልገባቸው ሀቅ ቢኖር ወቅቱ የቴክኒዮሎጅና የዲሞክራሲ ዘመን መሆኑን ነው ። እንኳንስ የአንድ ሀገር ሕዝብ ቀርቶ ዛሬ የዓለም ኅብረተስብ ሳይቀር ሳይንስና ቴክኒዮሎጅ ባፈራው የመገናኛና የመጓጓዣ ዘዴና ግልጋሎት እየተቀራረበና ሁለንተናዊ ልውውጥ በማድረግ የጋራ ችግሩን በማቃለል ላይ ይገኛል ። የኢንተር ኔትና ሌሎችም የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎቶች እንደ ህያው ምስክሮች የሚጠቀሱ ናቸው። በመሆኑም ነው ወያኔ ሊቆጠጣራቸውና ሊያግድ እየጣረ ያለው ። በዛሪይቱ ዓለማችን፥ ማነኛው ሀገር የቱን ያህል ኃያልና ሀብታም ነኝ ብሎ ቢመጻደደቅም፥ ብቻውን ተነጥሎ ሊኖር ከቶ አይቻለውም ። ይህም በመሆኑም የጋራ ገበያ፥የጋራ መከላካያ ፥ የጋራ ገንዘብ፥ የጋራ ኢኮኖሚና የሳይንስ ማኅበረሰብ ወዘተ እየመሰረተ ፥ የጋራ ችግሮቹን በጋራ ለማቃለል ይጥራል። የአደንዛዥ ዕፅዎችንም ሆነ ወንጀለኞች፥ ድንበር እየጣሱ የሚጓዙትን ተላላፊ በሽታዎች፥ አሸባሪዎችንና ገንዘብ ዘራፊዎችን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ፥ የዓለም ኅብረተስብ ፥ በግድ የጋር ጥረትና ትብብር እንደሚያስፈልገው ለክርክር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም። የዓለም ኅብረተስብ በዚህ ክስተት ውስጥ እየኖረ እያለ ፥ የወያኔ መሪዎች ግን በበርካታ ዘመናት በሂደት የተገነባውን የኢትዮጵያ ኅብረተስብ አንድነትና ኃይል በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት ከፋፍለው በቁርጥራጭ ክልል ተደይኖ እንዲኖር እያደረጉት ይገኛሉ። ይህን ዕቅዳቸውን የገለበጡት፥ የኢጣሊያ ፈሽስቶች ኢትዮጵያን ከፋፍሎ እየገዙ ለማጥፋት ከአወጡት የቅኝ ግዛት ካርታ ላይ ነው ። "የእሳት ልጅ አመድ " እንዲሉ፥ እነመለስ ዜናዊ ይህንን የሚፈጽሙት በትግራይ ሕዝብ ስም መሆኑ እንደ ታሪክ ምፀትና እንቆቅልሽ ሲጠቀስ የሚኖር መሆኑን ግን አላሰቡበትም ። ለኢትዮጵያ መሠረታዊና ዘላቂ ጥቅም የቆሙ ስለአልሆኑ ፥ የታሪክ ፍርድና የትውልድ መርገም ያስጨንቃቸዋል ተብለውም አይጠበቁም።

ይህ የያዘነው ምዕተ-ዓመት ተወደደም ተጠላ÷አነሰም አደገ÷ዴሞክራሲ በሂደት እየተከሰተ ያለበት ክፍለ ዘመን ነው ። ይህ የዲሞክራሲ ጮራ÷ “ጨለማው” ክፍለ-ዓለም ተብሎ በቅኝ ገዥዎች በተሰየመው የአፍሪካ አህጉር ሳይቀር እየፈነጠቀ ያለበትን ሂደት እያየን ነው። ለዚህ ማስረጃ ይምጣ ከተባለ÷ ደቡብ አፍሪካን ብቻ መጥቀሱ ይበቃል። የሚያሳዝነውና የኢትዮጵያን ሕዝብም እንደ እግር እሳት የሚያቃጥለው ግን ÷ ለመላው የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት የነበረችው ሀገሩ ዛሬ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት መሆኗ ብቻ ሳይሆን በሀገር በቀል ከሃዲዎች በብሄረሰብ ተከፋፍላ የሕልውናዋ ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ መግባቱም ጭምር ነው ።

እንግዲህ ዛሬ ኢትዮጵያን ማየትና መገምገም የምንችለው ÷ በጥንት ሁለንተናዊ ገፅታዋ የነበረውን ታሪኳንና ዛሬ በዚህ ትውልድ ዘመን ያለችበትን ሁኔታ እየተነተንን ÷ በወደፊት ዕድሏ ላይ ማተኮር ያለብን መሆናችን ነው ። ሀገር ሊያረጅ ይችላል ። ሀገር ሲያረጅ ደግሞ ጃርት ማብቀሉ አይቀርም ። ሀገሩ ጃርት ማብቀሏን የተገነዘብ ሕዝብ በበኩሉ ያዝናል ። የጎበዝ ያለህ ! የጀግና ያለህ ! እያለ ይማልላል ። ጀግና ተፈጥሮ የሀገርና የሕዝብ መድኅን እስከሚሆን ድረስ ግን ÷ ታሪክ ሀደ ባሻ ሆኖ አይጨነቅም ። ሁሉንም ይመዘግባል ። ታሪክ ያለው ሕዝብ በበኩሉ በታሪኩ ይኮራል ። ታሪክ ሰሪዎችም ÷ አኩሪ ታሪክ እየሰሩ ሀገር አድነው ያልፋሉ ። ከማለፋቸው በፊት ግን በኢትዮጵያ ጠላቶች ከርሰ-መቃብር ላይ የኢትዮጵያን ትንሣዔ ያበስራሉ ። ይህ የታሪክ ሀቅ ነው ። የሀገራችንም ታሪክ የዚህ ሀቀና ክስተት አንድ አካል አንድ አምሳል ነው ። ልብ ያለው ዜጋ ልብ ይበል ! ልብ የሌለው ልብ ይገዛ ! ታሪክ ቅርስ ነውና በከፋፋዮችና ዘመናዊ ባንዶች ሲጠቃ እንቃወም ÷ እንታገል ÷ ኃይላችንና ኅብረታችን አስተባብረን ሀገራችንን እናድን ! በታሪክ አተላዎች ከመገዛት ÷ ታሪክ እየሰሩ ማለፍ ÷ የጥንቱ የጧቱ ታሪካችን ነው !!

EthioLion.Com